## የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በአዋጅ ለመለወጥ የሚደረገውን በመቃወም በቶሮንቶ፣ ካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ፅህፈት ቤት ፒቲሽን ማስፈረም ጀመረ

በወያኔ ኢሕአዴግ ፓርላማ ለብዙ ሺህ ዓመታት የኢትዮጵያና የሕዝብዋ መለያ ሆና የቆየችውን የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 654/2001 ለመለወጥ መወሰኑን በመቃወም በአገር ቤት መጠነ ሰፊ የሆነ የተቃውሞ ድምጽ መኢአድ ከሕዝብ ጋር ሆኖ እያሰማ መሆኑን በዜና ማሰራጫዎች ተሰምቷል። የመኢአድ ፕሬዚዳንት ክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልም በተደጋጋሚ በዜና አውታሮች በሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ላይ ቃለ መጠይቅ ማድረጋቸው፣ መኢአድም የተቃውሞ መግለጫ ማውጣቱና ሕዝባዊ ስብሰባ በማድረግ የተቃውሞ ድምጽ እያሰማና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይመክርና ሳይወስን ማንም መለወጥ አይችልም በማለት ወቅታዊና ሕዝባዊ አጀንዳ ይዞ በመታገል ላይ ይገኛል።








በዚሁም መሰረት በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ጽህፈት ቤት በቶሮንቶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ለመቀየር የሚደረገውን በመቃወም በቶሮንቶ ከተማ ኢትዮጵያውያን የአዲስ ዓመት በዓልን ለማክበር በሚገኙበት ቦታ በመገኘት ለሕዝብ ጉዳዩን በማሳወቅ የፊርማ ማሰባሰብ ሥራ መጀመሩንና በዕለቱ በርካታ ኢትዮጵያውያን ድጋፋቸውን በማሳየት የተቃውሞ ፒቲሽን ላይ ስምና ፊርማቸውን ማኖራቸውን ጽህፈት ቤቱ አስታውቋል።









ቅንጅት የኢትዮጵያ የባሕልና የእርዳታ ድርጅት በቶሮንቶ (የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ በካናዳ) በዚህ የፊርማ ማሰባሰብ ሥራ በመጀመሪያው ቀን በጣም የተሳካና አጥጋቢ መልስ ያገኘ መሆኑን በመግለጽ የፊርማ ማሰባሰቡ ተግባር የሚቀጥል መሆኑንም አስታውቋል፡፡





ከሌሎች የበዓሉ ተሳታፊዎች መካከል በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ደምቃና
አሸብርቃ በምትገኘው ድንኳን ላይ የድጋፍ ድርጅቱ ስምና ዓርማ ተሰቅሎ፣ ደጋፊዎቹ በባሕል ልብስ ሆነው የሚመጣውን ሁሉ የመልካም አዲስ ዓመት ሰላምታቸውን እያቀረቡ ወያኔ/ኢሕአዴግ ሰንደቅ ዓላማችን ለመለወጥ በፓርላማው ያጸደቀ መሆኑን በማስረዳት የተቃውሞ ፊርማ ሲያሰባስቡ፤ ከጎኑ ደግሞ ሴቶች አባላት የቡና ረከቦት ላይ ስኒ ደርድረው የእጣኑ ሽታ ሃላፊ አግዳሚውን እየተጣራ ቡናው በአንድ በኩል ፈንድሻውና የቡና ቁርሱ ከጎኑ ሆኖ ይሰተናገዳል፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጠረጴዛው ላይ ከክቡር ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል የመኢአድ ፕሬዚዳንት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተላለፉት መልዕክት ጎላ ባለ ፅሑፍ ተቀምጦ፣ በድንኳን ውስጥ የተለያዩ የባሕል ስዕሎች ተለጥፈው በሞቀና በጋለ መንፈስ የድጋፍ ፅህፈት ቤቱ አባላት ስለ ሰንደቅ ዓላማቸው በመቆርቆር ፊርማ በማሰባሰብና ገለጻ በማድረግ በዓሉን በሥራ ሲያከብሩ ውለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሕጻናትም በአገር ቤት ድሮ እንደሚደረገው የአባባ ስዕሎችን በመሳልና ከለር በመቀባት እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሰዎ የሚል መልዕክትና ሰንደቅ ዓላማችንን በመሳል መልካም ምኞታቸውን ባሕላዊ በሆነ መልኩ በማቅረባቸው ብዙ ሰዎች የአገር ቤቱን ትዝታ እንደቀሰቀሰባቸው ገልጸዋል፡፡





የቶሮንቶው የድጋፍ ቻፕተርም ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሕዝቡን ለመድረስና ለማግኘት በአጭር ቀናት ውስጥ የወሰነ ቢሆንም ውጤቱ ከጠበቀው በላይ በመሆኑ በመደሰት በዝግጅቱ የተሳተፉ ሁሉ ደከመን ሳይሉ እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ተኩል ድረስ ቆይተዋል፡፡










በዚህ አጋጣሚ በጉልበት በገንዘብና በሃሳብ እንዲሁም የተቃውሞ ፒቲሽን በመፈረም የተባበሩትን ሁሉ ጽህፈት ቤቱ እያመሰገነ፤ የ2002 አዲስ ዓመት የሰላምና የድል ዘመን እንዲሆን በመመኘት ሁሉም ለሀገሩ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለሰንደቅ ዓላማው በአንድነትና በጋራ እንዲቆምና እንዲታገል ያሳስባል፡፡

በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ድጋፍ ጽህፈት ቤት

ቶሮንቶ
መስከረም 2 ቀን 2002